የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
Ginbot7 Movement for Justice Freedom and Democracy
Tel +44 208 1335670 pr@ginbot7.org

ሚያዚያ 27/2001 ዓ.ም

# ወያኔ በዘረኝነት ሰክሮ የሚፈጽመውን ወንጀል ለማስቆም ሁሉም ቆርጦ ይነሣ፡፡

‹‹መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደረገብኝ፡፡ ይቅርታ! መፍንቅለ መንግስት ሳይሆን በህዝብ የሚወደዱትን መለስ ዜናዊንና በረከት ሰምኦንን የመሳሰሉ ውድ ባለስልጣኖቼን ሊገድሉብኝ ነበር ›› በሚል ሰበብ ፣ አማራነትን የጥቃቱ ሰለባ አድረጎ ወያኔ በዋንኛነት በአማራ ክልል ውስጥ በመውሰድ ላይ የሚገኘውን ዘረኛ እርምጃ ግንቦት 7 አጥብቆ ይኮንናል፡፡ ሌሎችም ከእዚህ በፊት የተመሳሳይ ጥቃት ሰለባ የሆኑና ወደ ፊትም ተመሳሳይ የሆነ ዘረኛ ጥቃት የተደገሰላቸው መሆኑን የሚያውቁ የተለያዩ ድርጅቶችና የሀገሪቱ ዜጎች በሙሉ ይህን እኩይ ድርጊት ሊኮንኑት ይገባል፡፡

ይህ ዘረኛ ጥቃት አማራነትን ማአከሉ ያደረገ ቢሆንም በአማራነታቸው እየተጠቁ ያሉት የጦር መኮንኖችና የሲቪል ሠራተኞች ያነሱት ተቃውሞ ‹‹በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጥቂት ዘረኞች የሚፈጸሙት ጭፍጨፋ፣ የመብት ረገጣና ከፍተኛ የሃብት ዘረፋ ያብቃ›› የሚል ነውና ስቃያቸውና መከራቸው ለሁሉም ዜጎች የተከፈለ መስዋእትነት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተለይ ወያኔ በአደባባይ ሊነግረን ያልፈለገው በአማራነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት እየተፈጸመ የሚገኘው፣ በሺዎች የሚቆጠሩ በሥራ ላይ ያሉና ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ጥያቄ በማንሳታቸው ከሥራ ገበታቸው በግፍ የተቀነሱ ወታደሮችና የሲቪል ሰረታኞች እየታሰሩ፣ እየተቀጠቀጡና እየተሰደዱ ያሉት በወሎ፣ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በሰሜን ሸዋና በአዲስ አበባ ከተማ እንደሆነ ለማወቅ ችለናል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረውም ህዝብ ይህንን ዘረኛ የሆነ የወያኔ ጥቃት ላመስቆም በአንድነት መነሳት ይኖርበታል፡፡ የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት እስከ እለተ ህልፈታቸው በእሽክርና ለማገልግል የቆረቡትን ሆዳም የብአዴን መሪዎች በቃችሁ አጠገባችን አትድረሱ ሊላቸው ይገባል፡፡ ወያኔ የጀመረውን ዘረኛ ጥቃት እንዲያቆም፣ ያሰራቸውን ባስቸኳይ እንዲፈታ፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብና በተለይ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው የአማረው ክልል ህዝብ፣ ተማሪው፣ ገበሬው፣ ሠራተኛውና ነጋዴው፣ ወጣቱና አዛውንቱ በተለያዩ መንገዶች ቁጣውን ለመግለጽ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ በደረሰው መረጃ መሠረት ወያኔ የእርሱን ዘረኛ አገዛዝ ለመፈታተን ወኔው ከሌላቸው ጥቂቶች በስተቀር የተቀሩትን በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙትን አማሮች በሙሉ በአደገኛነት የፈረጃቸው መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡ በሠራዊቱ ውስጥ ለወያኔ ሥጋና ነፍሳቸውን ሸጠዋል ብሎ ከሚያስባቸው በጣት ከሚቆጠሩ አማሮች በስተቀር በአስር ሺዎች የሚቆጠሩትን የሠራዊቱን አባላት ከማሰር አንስቶ ከሥራ በማባረር የዘር ማጥራት ሥራ ለመስራት ወያኔ ያቀደ መሆኑን ደርሰንበታል፡፡

ይህ እኩይ የወያኔ እቅድ ተፈጻሚ እየሆነ የእያንዳንዱን የጦር መኮንንና ወታደር ቤት ከማንኳኳቱ በፊት ሁላችሁም በግል ይሁን በተናጠል መብታችሁን ላለማስነጠቅ በጊዜ ጥንቃቄ እንድታደርጉ ራሳችሁን፣ ባልደረቦቻችሁንና ወገኖቻችሁን የመከላከል እርምጃ እንድትወስዱ ግንቦት ሰባት ያስገነዝባችኋል፡፡ የወያኔን ከዘረናኛነት የሚመጣ ጨካኝነት አብራችሁ በመስራት የምታውቁት ስለሆነ የተደገሰላችሁ የዘር ማጥራት ሥራ መጨረሻው ምን እንደሚሆን የምትሱት አይመስለንም፡፡ በታረካችሁ የሌለን ተንበርካኪነት እንደመልካም ሸማ እንድትለብሱ ወኔ ቢስ የአድርባይነት ምክራቸውንና የፈሪ ማስጠንቀቂያቸውን የሚተፉባችሁንና ራሳቸውን አዋርደው የውርደት እድር አባላቸው ሊደርጓችሁ የሚፈልጉትን በሙሉ ‹‹ዞር በሉ ከፊቴ ›› በሏቸው፡፡ ለራሳችሁ መብት፣ ለቤተሰቦቻችሁ፣ ለአከባቢያችሁና ለመላው ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ መብት ቁሙ፡፡ ምርጫው በዘረኞቹ ወያኔዎች የዘለላም ባርነት ሥር መውደቅ ወይም ሞት ከሆነ ደግሞ ሞትን ሺ ጊዜ እንድምትመርጡ ነጻነትን ለማያውቁት ነጻ አውጪዎች በተግባር አሳይዋቸው፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ለእናንተና እንደ እናንት ‹‹አምቢ ለመብቴ! እምቢ ለነጻነቴ!›› በማለት በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል ከሚነሳ ወገናችን ጎን ሁሌም ይቆማል፡፡ በሚቻለው ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ‹‹እምቢ ለዘረኛ አምባገነኖች! እምቢ ለዘራፊዎች!›› በማለት ለሚያደርገው ትግል ግንቦት 7 ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል፡፡

በእዚህ አጋጣሚ ይህ ከቁጥጥር ውጭ በመውጣት ላይ የሚገኝን፣ መለስ ዜናዊና ጥቂት ዘረኞች ህዝብን በዘር እየለዩ የሚወስዱትን የማጥቃት እርምጃ፣ ይህ ድርጊት ለዘመናት አብሮ በኖረ ህዝብ መካከል ጥሎ የሚያልፈውን ቂም የምትገነዘቡ በዘረኛነት ያልተለከፋችሁ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት፣ የወያኔ ፖለቲካ ድርጅት አባላት እንዲሁም ሌሎች የትግራይ ልጆች ይህን የዘር ማጥራት ተግባር በግልጽና በአደባባይ እንዲኮንኑ ጥሪ እናቀርባለን፡፡ ጥቂት የወያኔ ባለስልጣናት በወያኔ አባላት ስም በጦር ወንጀልና በዘር ማጥፋት የሚያስጠይቅ ዘግኛኝ ወንጀል እየፈጸሙ፣ አሁንም በእዚሁ የጥፋት ጎዳና

ሲነጉዱ « በእኛ ስም አይደረግም» የሚል ተቃውሞን አለማሰማት በዝምታ በተደረገ የተባበሪነት ወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን ወቅቱ ሳይረፍድ ልናስታውሳቸው እንወዳለን፡፡

ግንቦት ሰባት የፍትሕ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
ሚያዚያ 27/2001 ዓ.ም